# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 17

ግንቦት 7 ቀን 2014ዓም(15-05-2022)

አገር እንዴት ሰነበተች የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስንነሳ መልሱን በሚከተለው ሃረግ ውስጥ ተጠቅሎ እናገኘዋለን።አሁንም ላለፉት 31 ዓመታት ቀስፎ በያዛት የጎሳ ፖለቲካ የተከለው ሥርዓት ሳይወገድ ካደረሰባት ውድቀት ትድናለች ማለት ዘበት ነው።ስለሆነም ከነበረችበት ሁኔታ አሁንም የተላቀቀች ወይም ከሚሻል ደረጃ ላይ የደረሰች ሳይሆን ይበልጥ ተባብሶ ከድጡ ወደማጡ የመሄዱ ነገር ፍጥነቱን ጨመረ እንጂ አልቀነሰም።

ሁለገብ ሁኔታውን በዝርዝር ከማቅረብ ይልቅ ለዚህ ላለችበት አሳሳቢ ደረጃ ያበቃት የጎሰኞች አገር ጠል ስብስብ መሆኑ በተደጋጋሚ ላለፉት ብዙ ዓመታት በማስረጃ የተደገፈ፣በጥናት የተሰላ በቂ ዝርዝር ተሰጥቶበታል።የችግሩን ምንጭ ማወቅ ብቻም ሳይሆን መፍትሄዎችም ቀርበዋል።ብዙዎች የሚስማሙበትና እስከአሁንም ድረስ የሚጠይቁት አገራችንን ካለችበት መቀመቅና አደገኛ ደረጃ ለማውጣትና አንድነቷን አስከብሮ የሕዝቧንም ስቃይ ለማሶገድ መፍትሔው ብሔራዊ አንድነት ያለው ሕዝባዊ ሃይል መፍጠርና የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ነው የሚለውን ሃሳብ የሚተካ ወይም የሚቀይር አማራጭ አልተገኘም፤ሊገኝም አይችልም።የኢትዮጵያ ጠላቶች ተባብረው ሲያጠቁ ሌላው አገር ወዳድ ተባብሮ መቆም ካልቻለ በተናጠል የአደጋው ሰለባ ከመሆን አያመልጥም።ለዘመናት ያደረገው በቅጡ ያልተደራጀና ግብታዊ ትግል ግቡን ሊመታ ያልቻለውም በዚሁ ድክመት የተነሳ ለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፤መስማማት ብቻም ሳይሆን ከተመሳሳይ አሮንቋ ለመውጣት በተደጋጋሚ ድምጻቸውን አሰምተዋል፤እኛም ስናሰማ ኖረናል።

የጠላቶች መጠናከር የሚጀምረው ሊታገላቸው የሚችለው ጎራ በኩል መሪ ድርጅት ሳይኖር፣ በሥልጣን፣በጎጥና በሃይማኖት ድክመትና መፈረካከስ ሲኖር እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ለዚያም ሳይታክቱ ተግተው ይሠራሉ።በመንግሥትነት ስም ሁሉንም በመቆጣጠር ማለትም የመገናኛውን ዘርፍ፣ የገንዘቡን ምንጭ፣የመከላከያ ሃይሉን በመቆጣጠር ካላቸው የሃይል ሚዛን ብልጫነት በተጨማሪ ቀላሉና እርካሹ ዘዴ በጠላታቸው ውስጥ ሰርገው በመግባት አለያም ለጥቅም የሚገዙ የውስጥ አርበኞችን በመመልመልና በመደለል ተቃዋሚያቸውን ለማድከም የሚጠቀሙበት ስልት የተለመደ ነው።ይህ እንደ አንዱ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የውጊያ ስልት ነው።በአገራችን ኢትዮጵያም በሥልጣን ላይ የተቀመጡት አምባ ገነኖች ሲጠቀሙበት ኖረዋል። ያሁኖቹም ካለፉት በበለጠ ጊዜውና እውቀቱ ባፈራቸው መሳሪያዎች ታግዘው ይህንኑ የመበታተን ስልት እዬተጠቀሙበት ይገኛሉ።

ሌላው በአገር ደረጃ ድህነትና ችግር ሲፈጠር ሕዝቡ የሚልስ የሚቀምሰው ሲያጣ የሚከሰተው የእርስ በርስ መናቆርና መጨታጨቅ ብሎም እራስን የማዳን እሩጫ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የሚገኝ የበላይነት ነው።ይህንንም በሥልጣን ላይ ያሉ አረመኔዎች ይጠቀሙበታል፤እርሃብን እንደ ጦር መሣሪያ ይገለገሉበታ ማለት ነው።የእለት ጉርሱን የሚያገኝ ሕዝብ በተረጋጋ መንፈስና አይምሮ ሌላ ጉዳይ በተለይም ስለሃገሩ እድገትና ስለተሻለ ሥርዓት ማሰቡ ስለማይቀር ለዚያ እንዳይበቃ ለሆዱ ብቻ እንዲያስብና እንዲያሰላስል፣በፍርፋሪ ሰጥ ለጥ እሺ ጌታዬ! ብሎ ሊገዛ እንደሚችል አድርጎ መያዝ የተሻለ ነው ብለው ያምናሉ።

ሌላው ሕዝብን በውሸት ፕሮፓጋንዳ አደንቁሮ ተከታይና ደጋፊ ማድረግ ሲሆን የተሻለ ግንዛቤ ያለውን ደግሞ በሚፈልገው ደካማ ጎኑ ገብቶ ተከታይ ማድረግ ነው።ስልጣን የሚፈልገውን በሥልጣን፣ገንዘብ የሚፈልገውን በገንዘብ፣መሬትና ቤት የሚፈልገውንም በዚያው ፍላጎቱ ተብትቦ መያዝ ነው።

አምባገነኖች ሕዝቡን በጎሳ ማንነትና በሃይማኖት ለያይቶና የክልል ወሰን ዘርግቶ እርስ በርሱ ማባላትም አንዱና ቀላሉ ስልትታቸው ነው።በእኛ አገር ፣በኢትዮጵያ ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው ዘዴዎች ተጠቅሞ ሥልጣኑን የያዘው ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አንድነት የሆነ ጎሰኛ ቡድን ይኸው 31 ዓመት ሞላው።አሁንም የልዩነት መርዝ የመርጨት እብደቱ ቀጥሏል።የመርዙን ዋንጫ ያልተቀበሉ አገር ወዳዶች እምቢ አሻፈረን በማለት ብዙ መስዋእትነት ከፍለዋል።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፋኖ በሚል ስያሜ ሕዝባዊ ሠራዊት ፈጥረው ለአገራቸው ህልውናና ለራሳቸው ክብር ሲዋደቁ ቆይተዋል።ጥቂት የማይባሉም የህይወት ዋጋ ከፍለዋል፤አሁንም እዬከፈሉ ይገኛሉ።ይህ የሕዝብ እምቢተኝነት ያልተዋጠለትና ያሰጋው መንግሥት ነኝ ባይ የጎሰኞች ስብስብ ለመከፋፈል ያልሞከረው ሴራ የለም። በሃይል ሞክሮ አልተሳካለትም፤በገንዘብና በጥቅም ሞክሮ አልተሳካለትም፣በጎጥ ለመከፋፈል ያደረገው ሙከራም እንዲሁ ውጤት አልባ አድርጎታል።አሁን ደግሞ በሽልማትና በእውቅና ስም ለመለያዬት ያቀደው ስልት ይበልጥ እራሱን አጋልጦታል።ለሕዝባዊው ሠራዊት ወይም ፋኖ መፈጠር ምክንያት የሆነው በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረውና ለጎሰኞች አገር የማፍረስ ሴራ የማይመቼው በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰው የተቀናጀ፣በመንግሥት መዋቅርና እውቅና የተደገፈ የመከራ ውርጅብኝ ነው።አማራው ከራሱ በላይ ኢትዮጵያን በመውደዱ በጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ዘንድ ዋና ጠላት ተደርጎ ተወስዷል።የውጭና የውስጥ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚረባረቡት አማራውን በማጥፋት ዘመቻ ላይ ነው።የውጭ ጠላት ኢትዮጵያን ለመውረር ሲያስብ ጣቱን የሚቀስረው በአማራው ላይ ነው። ይህንን የጣምራ ጠላት ዘመቻ ለመመከት የአማራው ልጆች እምቢ አሻፈረኝ በማለት ዱር ቤቴ፣ለኩልነቴ፣ ለነጻነቴ፣ለኢትዮጵያዊነቴ ብለው ተነስተዋል።

ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ወያኔ ሃይሉን አሰባስቦ ጥቃት የከፈተውና ወሮም ብዙ ወንጀሎችን የፈጸመው በአማራው ላይ ነበር፣ እንዲወር መንገዱን ያመቻቸለትና የአማራውን መወረር እንደ በጎ ዕድል የቆጠረው በአብይ አህመድ የሚመራው የኦነግ -ኦሕዴድ መንግሥት በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል በሚደርሰው ቀውስ እራሱን ተጠቃሚና የበላይ አድርጎ የማዬት ህልም አድሮበት ነበር።ግን ሕልሙ ወደ ቅዢት ተለወጠና በሥልጣን የተዋጋው ወያኔ ጣምራ በር ደርሶ አዲስ አበባን ሊቆጣጠር ጥቂት ሲቀረው ከሥልጣኑ ለመባረር አደጋው ከፊቱ ድቅን ሲልበት ቀድሞ ድረስልኝ ያለው የአማራውን ሕዝብ ነበር።ምንም እንኳን ሴራውን ቢረዳውም ፣ወያኔን ለመቅጣት ሲል የሆዱን በሆዱ ይዞ ጥሪውንም ሰምቶ ከውድቀት ያዳነው ይኸው የአማራው ፋኖ ሕዝባዊ ሠራዊት ነበር።አብይ አህመድ ግን የሥልጣን መንበሩን ካዳነ በኋላ መልሶ ለማጥቃት የተነሳው አማራውን ሆነና አረፈው። አማራውም ባጎረስኩኝ እጄን ተነከስኩኝ ብሎ ዳግመኛ ላለመታለል ቃል ገብቶ ተነሳ።ልጆቹም ከዳር እስከዳር በፋኖነት ተሰለፉ።

ይህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እያደገና ተሰሚነት እያገኘ የመጣውን ሕዝባዊ ሃይል ፋኖን በማጥፋት አማራውን ካለማንም ተከላካይና ዋቢ ባዶውን ለማስቀረትና ጭቆናውን ለማስቀጠል ጦሩን ከተት ብሎ ዘመተበት። በእጃዙር ዘዴ ለመበታተንና እርስ በርሱ ለማጋጨት ይረዳኛል ብሎ ያሰበውን ሁሉ አደረገ፣ግን አልተሳካም።በቅርቡ ደግሞ በሽልማትና በእውቅና ስም ለማጥመድ ያቀደው ሸርጉድ ቅ ገና ከጅምሩ ውድቅ ሆኖበታል።በዚህ የዘገዬ ሩጫ የእኔ ናቸው ወይም ለእኔ ይቆማሉ ብሎ ያሰባቸውን የተወሰኑ ታጋዮች ለመደለል ሲሞክር በአብዛኛው ግን የራሱን የሥርዓቱን ዋና አገልጋይ የሆኑትን በአማራው ስም የሚነግዱትን ሸጦ በሌዎች በወርቅ ኒሻን ሲያሽቀጠቁጣቸው ታይቷል።እነዚህ ይሉኝታ

ቢስ ከሃዲዎች በአማራው ስም ሥልጣኑን በመያዝ ቀደም ሲል ለ27 ዓመታት የወያኔ መራሹ ኢሕአዴግ ፣ላለፉት አራት ዓመታት ደግሞ ለኦነግ-ኦሕዴድ መራሹ ብልጽግና ያደሩ ምስለኔዎች በመሆን ላሳዩት የአድር ባይነት ማረጋገጫ የተሰጡት ሽልማት እንጂ ለሕዝቡ በሠሩት ውለታ እንዳልሆነ እንኳንስ ሕዝቡ እነሱም በሚገባ ያውቁታል።በጀግንነት ሳይሆን በሌብነት ባሳዩት ትልቅ ስርቆት የተሰጣቸው ሽልማት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።አንዳንድ የዋሆች ፋኖ እገሌ ለምን አልተሸለመም፣ለምንስ እውቅና አላገኘም ሲሉ ይሰማሉ ግን ፋኖ ከሚታገለው አገር አፍራሽ ቡድን እውቅናም ሆነ ሽልማት አይሻም፤የሱ ሽልማት  የጎሰኞች ስርዓት መወገድ ነው።እውቅናም ከሕዝቡ እንጂ ከጎሰኛ አምባገነኖች አይጠብቅም።  እውነተኛ የሕዝቡ ልጅማ በነዚሁ አድርባይ ምስለኔዎች እየተሳደደ ትጥቁንም ስንቁንም እዬተነጠቀ ይገኛል።ፋኖና ልዩ ሃይል ናቸው የተባሉት ቀርተው ይደግፋሉ የተባለ የአማራው ተወላጅ በነቂስ የመከራ ገፈታ እዬቀመሰ ይገኛል።እንደ ጥገት እዬታሠረ እዬተፈታ የስቃይ ኑሮ እዬመራ ነው። በሁሉም የኢትዮጵያ መሬት አገሬ ናት ብሎ ሠርቶ የሚያድረው ዜጋ በአማራነቱ ብቻ ወይም በሚያመልከው እምነት ተለይቶ መገደል፣መፈናቀል መቁሰልና መዘረፍ የእለት እለት እጣፈንታው ከሆነ ውሎ አድሯል።

ለጎሰኛው መንግሥት ስጋት የሆነበት አገሬ ኢትዮጵያ እኔ እያለሁ አትፈርስም ብሎ በግንባር ቀዳሚነት የቆመው የአማራው ማህበረሰብ ስለሆነ ለአገር አፍራሾቹ ዋና ጠላት ተደርጎ ተወስዷል።ሌሎቹም አገር ወዳዶች ከአማራው ጎን የተሰለፉ እንዳሉ ባይካድም በጣም ጥቂቶች ናቸው።ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ማወቅ የሚኖርባቸው ቢኖር የአገር አፍራሾቹ ቡድን  ሴራ በአማራው ላይ ብቻ እንደማይቆምና ነገ የነሱም ተራ ሊሆን እንደሚችል ነው።አመላካችም ብዙ ድርጊቶች ታይተዋል።ልብ ያለው ልብ ሊል ይገባዋል።ማነህ ባለሳምንት የሚሉት የእቁብ ተረኛነት ይዘት ያለው አካሄድ መሆኑን መረዳትና መዘጋጀት ያስፈልጋል። በመንግሥት ቅስቀሳና በጠባቦች ጋጋታ ተታሎ በጭቁን የአማራው ተወላጅ ላይ የጥቃት እጅ መሰንዘር ነገ ለማይወጡት ፍዳና መከራ ይዳርጋል።

በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው ሕዝብ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ከዚህ የመከራ ኑሮ ሊገላግለው የሚችለው መንገድ ሃይሉን አስተባብሮ በጥቅም ሳይደለል፣በፍርሃት ሳይርድ፣ለጋራ ሃገር ሲል ቤቴ ንብረቴ ወይም ህይወቴ ሳይል  በዱር በገደል በመፋለም ላይ ያለውን የፋኖን ሕዝባዊ ጦር መቀላቀል ብቻ ነው።በዚህም ብቻ ሳይወሰን ለአገሪቱ የሚመጥን ለሕዝባዊ መንግሥት እርሾ የሚሆን የጊዜያዊ መንግሥት አቋቁሞ ትግሉን በተቀናጀ መልኩ ማስኬድ አስፈላጊ ነው።አገር በውጭ ሃይሎች ሲወረር ወይም በአምባ ገነኖች መዳፍ ሥር ሲወድቅ የነጻነትና የዴሞክራሲ ሃይሉ በሚያመቸው ቦታ የራሱን መንግሥት መሥርቶ መታገሉ አዲስ ነገር አይደለም።መንግሥትና ሥርዓት ለመቀዬር የሚተካውን የመንግሥት ቁመና በትግሉ ውስጥ ሆኖ መፍጠርና ማጠናከር የግድ ይላል።ቋሚ መንግሥት ከድል በኋላ፣ሰላምና መረጋጋት ሲፈጠር በሕዝቡ ምርጫ የሚፈጠር ቢሆንም በትግልም ወቅት እንደ መንግሥት የሚያገለግል ማዕከል መኖር የትግሉ ስኬት ማረጋገጫ ይሆናል። የወያኔ አሸባሪ ቡድንም ሆነ የኦነግ ኦህዴድ መራሹ ቡድን እራሳቸውን በመንግሥት ደረጃ ሰይመው ጥቃት ሲያደርሱ ተጠቂው ብዙሃኑ ሕዝብ የእኔ ነው የሚለውን መንግሥት አለመመስረቱ ለጠላቶቹ ብትር የተመቸ ያደርገዋል።ስለሆነም የመከላከያና የድርጅታዊ እንቅስቃሴውን የሚመራና የሚያስተሳስር አንድ የጋራ አካል መፈጠር አለበት።ትግል ያለ ድርጅት፣ድርጅትም ያለዓላማና መርሃግብር ግቡን አይመታም። ቢሞክሩትም መጨረሻው ስርዓተአልበኝነትና የእርስ በርስ የጎበዝ አለቆች የሚፋጁበት ግርግር ይሆናል፤ ይህንንም በሥልጣን ላይ ያለው አገር አጥፊ ቡድን ስለሚፈልገው ያባብሰዋል። በተደጋጋሚ የሚሰማው የሕዝብ ጩኸትም ይኸው ነው።እኛም ደግመን ደጋግመን የምናሰማው ጩኸት ይኸው  የሕዝባዊ ጦሩን የሚመራ የጋራ አመራርና ድርጅት ይኑር ነው።የጋራ አመራር ያለው ድርጅታዊ መዋቅር ካለ የሚደረገው ድጋፍም ሆነ ተሳትፎ በቀላሉ ያድጋል።እንዴትና በማን በኩል ልርዳ የሚለውንም ጥያቄና

ጥርጣሬ ያሰግዳል።አሁን የሚታዬው በተበታተነ መልኩ የሚደረገው እሩጫና የገንዘብ አሰባሰብ ዘዴ ስጋትና ጥርጣሬ ከመፍጠሩ በቀር የብዙዎችን ቀልብ የሚስብና የሚያስተማምን  አይደለም።ስጋቱም ምክንያተ ቢስ ሳይሆን ባለፉት ጊዜያቶች በተደጋጋሚ ከታዩ ስህተቶች በመነሳት ነው።ዳግም ስህተት እንዲፈጠር አያሻም።የጥቅም ግጭትና ንትርክም የሚነሳው ድርጅታዊ ቅርጽና አሠራር በሌለበት ቦታ ነውና አላፊነት የሚሰማው በሁሉም ይውንታ ያገኘ  ትግሉንም ሆነ የትግሉን ሂደት፣ስትራተጂና ስልት ቀያሽ፣የሠራዊቱን አሰላለፍ፣የስንቅና ትጥቅ፣የግንኙነትና መረጃ እንዲሁም ገቢና ወጭ መቆጣጠር የሚችል መእከላዊ አካል መፍጠሩ ለስኬቱ ዋስትና ይሆናል።አገር በስርዓት እንድትመራ የሚሻና የሚታገል ሃይል ትግሉን በሥርዓት ለመምራት ፍላጎት ከሌለውና ካልቻለ ውጤቱ ያው በገሌ ይሆናል።

በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ቀና አገር ወዳዶች የሚያደርጉት መነሳሳት የሚደገፍ ቢሆንም በተለያዬ ቡድን በመሆኑ የድካማቸው ዋጋ ከንቱ እንዳይሆን ቢያስቡበት እንላለን።በተለይም የፋኖ አደረጃጀት አገር አቀፍ እንደመሆኑ መጠን በየከፍላተሃገሩና በየቀውራጃው ስም ተደራጅቶ ገንዘብ መሰብሰቡ የአንድነቱን ድርና ማግ ያቀጭጨዋል፣ለጠላትም አመቺ ዒላማ ይሆናል። አንድ አመራር፣አንድ ዓላማ ያለው  ሕዝባዊ ሠራዊት(ፋኖ)እንዲፈጠር ሁሉም የበኩሉን እንዲያበረክት የተደጋገመ ጥሪያችንን ዛሬም እናሰማለን።

አምባገነኖች ሊወገዱና የሥልጣን ዕድሜያቸው ሊያጥር ሲል የሚጫወቱት የመጨረሻ ካርድ ቢኖር ጦርነት መቀስቀስ ነው።ከጎረቤት አገር ጋር ወይም በሕዝብ መካከል ግጭት በመፍጠር የሕዝቡን ለለውጥ የመነሳሳት አቅጣጫ ለመቀዬር ይሞክራሉ።ለጥቂት ጊዜ ሊሳካላቸው ቢችልም ውሎ አድሮ ግን ከውድቀት አይድኑም።ምክንያቱም ጦርነቱ ይዞት የሚመጣው ተጨማሪ ችግር እንጂ የነበረውን ችግር አያጠፋውምና ነው።አሁን በወያኔና በኦሕዴድ በኩል የጦርነት ነጋሪት እዬተጎሸመ ነው።እነዚህ ጸረ ሕዝብ የሆኑ ተደጋጋፊ ቡድኖች በሚመሩት ሕዝብ ላይ ያደረው ምሬትና ብስጭት ሊያጠፋቸው ሲቃረብ የመጨረሻ መዳኛና መውጫ የማርያም መንገድ የሚሆናቸው ጦርነት ማወጅ ነው።በቀውስ መኖር የለመዱት እነዚህ ቀውሰኞች ካለጦርነት አይኖሩም።የትግራይም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጦርነት ለመዳንና ፣ከሚገፋው አስከፊ ኑሮ ለመውጣት እነዚህን አምባገነን ቡድኖች ከጫንቃው ላይ ለማውረድ በአንድነት ሲመክርና ሲታገል ብቻ ነው። ለዚያም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ዛሬ ነገ ሳይባል መጀመር ይኖርበታል።ለዚህ ተግባር በነጻነት የሚንቀሳቀሱት በውጭ አገር የሚኖሩ የትግራይና የሌላው በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ተወላጆች ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል።

መንግሥት ተብዬው ከሃዲ ቡድን ከወያኔና ከምዕራባውያን በተለይም ከአሜሪካ ጋር ለመታረቅና የሚፈልገውን የገንዘብና የመንግሥታዊ እውቅና ለማግኘት የወልቃይትንና የራያን ለም መሬት አሳልፎ ለመስጠት ዳር ዳር እያለ ይገኛል።ለስሙ ለጦርነት ዝግጁ ነኝ ቢልም ሽማግሌ ገብቶበት የእርቅ ጭዳ አድርጎ ሊያቀርብ ያሰበው ወልቃይትንና ራያን ለመሆኑ በሕዝበ ውሳኔ ይፈታ የሚለው የሁለቱም የመፍትሔ ሃሳብ  በመካከላቸው ያለውን ምስስልና መተጋገዝ ያሳያል።ለዚያም እንዲያመች በከባቢው ለረጅም ጊዜ ተመድቦ፣ቦታውንና ማህበረሰቡን የሚያውቀውን የተደራጀ ጦር አንስቶ ቦታውን ወና ማድረጉ ወያኔ ሰተት ብሎ እንዲገባና ቦታዎቹን እንዲቆጣጠር የተደረገ ስምምነት ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም።ይህንን ተንኮል አንዳንድ የሥርዓቱ ደጋፊ የሆኑ ምሁራን ሲደግፉት ይሰማል።እነዚሁ በምሁር ስም የሚነግዱ ከንቱዎች የሚሰጡት ምክንያት ከመንግሥት በኩል የሚሰጠውን በመድገም ነው።ፋኖን መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣ፣እንደ ጠላት ወራሪ ወታደር ሲያዝበት እያዩና እዬሰሙ፣ የመንግሥት አፈ ቀላጤ  ከመሆን በላይ ቅሌት የለም።እነዚህ ምሑራን አብዛኞቹ አሜሪካ የሚኖሩ የአማራው ተወላጆች  ሲሆኑ አገር ቤት ወጣ ገባ እያሉ ለሚያገኙትትኙት መስተንግዶ ወይም እናገኛለን ብለው ለሚቋምጡለት ሥልጣን ወይም ልዩ ጥቅም ቤትና መሬት እራሳቸውን የሸጡ ናቸው።በፋኖም

ላይ የተመዘዘውን የጥፋት ሰይፍ ከመሳል ወደኋላ አይሉም።የትጥቅ ማስፈታቱን ዘመቻም ለሰላም የሚደረግ እርምጃ ነው ብለው ያምናሉ።እነዚህ ጉደኞች ልማዳቸው ከመጣው ጋር መንጎድ ስለሆነ በየጊዜው ቆባቸውን ለመለወጥ አይከብዳቸውም፤ይሉኝታ ቢሶች ናቸው።

አሁን አገራችን በወሳኝ ደረጃ ላይ ትገኛለች።የሕዝቡ ምሬት ገንፍሎ በመውጣት ላይ ነው።ፋኖን አትንኩብኝ እያለ ከመንግሥት ጋር ትንቅንቁን ይዞታል።የኑሮ ውድነቱ ትዕግስቱን አስጨርሶታል፣ ሰላምና ፍትሕ ማጣቱ በመንግሥት ላይ እምነት አሳጥቶታል።በመንግሥትና በባለሥልጣኖቹ በኩል የሚታዬው አስረሽ ምችው ድግስ፣በስበብ ባስባቡ የሃብት ብክነት፣ስርቆት፣ሌላም ሌላውም ተጨምሮ አደባባይ በመውጣትና ተባብሮም መግለጫ በማውጣት የለውጥ ያለህ እያለ ነው።የኦሮሙማው እብሪትና ተረኝነት ሁሉንም አንገሽግሾታል፤መንግሥትና ተባባሪዎቹም ሕዝቡን ለመከፋፈል የሚዘረጉት ወጥመድ እዬበዛ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም፣አንዱ ሲከሽፍ ሌላ እዬተመዘዘ የማወናበዱ ሥራ ተቀጥሎበታል።የውስጥና የውጭ ጠላቶች ከመቸውም ጊዜ በበለጠኢትዮጵያን ለማፈራረስ አሰፍስፈው የቆሙበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።እንዳይሳካላቸው ለማድረግ የግድ አንድ የትግል ማዕከል መፍጠር ያስፈልጋል።ይህ የተጠራቀመ የሕዝብ ብሶት ሱናሚ ሆኖ ጠራርጎ ለመውሰድ ጊዜው የቀረበ ይመስላል። ይህ የለውጥ ጎርፍ አቅጣጫውን እንዳይስት የሚመራ አካል መፍጠር ያስፈልጋል።

ሕዝባዊ ትግሉ በሕዝባዊ መንግሥት(ኮሚቴ) ይመራ!

ፋኖን ማሳደድና ትጥቁን ለማስፈታት መሞከር ዋጋ ያስከፍላል!!እኛም ፋኖ ነን!!